10ኛ አመት ቁጥር 46
10th Year No 46

ባህር ዳር ሚያዝያ 3 ቀን 1997 ዓ.ም
Bahir Dar April 11, 2005

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

# ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE HIG

## OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE
## IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA



| የአንዱ ዋጋ ብር Price | በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የፖ.ሣ.ቁ 312 P.o. Box |
|---|---|---|---|



| ማውጫ | CONTENTS |
|---|---|
| ደንብ ቁጥር 30/1997 ዓ.ም. | Regulation No. 30/2005 |
| በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የደብረ ብርሃን ጤና ሣይንስ ኮሌጅ ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ም/ቤት ደንብ | The Amhara National Regional State Debre Berhan Health Science College Establishment, Council of Regional Government Regulation. |

## ደንብ ቁጥር 30/1997 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የደብረ ብርሃን ጤና ሣይንስ ኮሌጅን ለማቋቋም የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ

በክልላችን በየደረጃው የሚያስፈልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት ለማሟላት ከተጀመሩት የ10+1፣ የ10+2 እና የ10+3 የጤና ሙያ ስልጠና

## REGULATION No. 30/2005

A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE ESABLISHMENT OF THE DEBRE BERHAN HEALTH SCIENCE COLLEGE IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

Whereas, besides expanding those institutions designed to train the middle-level health professionals in the already-started 10+1, 10+2 and 10+3 health

መርሀ-ግብሮች አንፃር የመካከለኛ ደረጃ ጤና ባለሙያዎች የሚሰለጥኑባቸውን ተቋማት ከማስፋፋት ጎን ለጎን የስልጠናውን ቀጣይነት ይበልጥ ማጐልበት ተገቢ መሆኑ ስለታመነበት፤

professionals' training programs with the view to meeting the needs for trained manpower required at any level in our regional state, it is believed appropriate to further strengthen such sustainability of such training;

ይህንኑ ዓላማ ከግብ በማድረስ በክልሉ ውስጥ በመካከለኛ ደረጃ በጤና ሙያ የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጐትን ለማሟላት፤ በሽታን በመከላከል ላይ ያተኮረውን የጤና ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረግና መንግስት በሁሉም መስኮች የቀየሳቸውን የልማት ስትራቴጅዎች በሚገባ ማስፈፀም በማስፈለጉ፤

Whereas, it is necessary to implement the health policy focusing on disease-prevention as well as duly execute the development strategies devised by the Government in all streams in order to fulfill the requirements for trained manpower, through accomplishing the said objective;

የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 እና በብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱ፡ አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 26 ድንጋጌዎች ሥር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

Now, therefore, the Council of the Amhara National Regional Government, in accordance with the powers vested in it under the provisions of art. 58 sub art. 7 of the revised Regional Constitution and article 26 of the National Regional executive bodies re-organization and determination of powers and duties proclamation N°.60/2001, /as amended/, hereby issues this regulation as follows:

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

## PART ONE
## GENERAL

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የደብረ ብርሃን ጤና ሣይንስ ኮሌጅ ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ም/ቤት ደንብ ቁጥር 30/1997 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 1. Short Title

This regulation may be cited as "The Debre Berhan Health Science College Establishment, Council of Regional Government Regulation No. 30/2005."

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው

### 2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this

ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "የአካዳሚክ ሠራተኛ" ማለት ከማስተማር፣ ከምርምርና ከሥርዓተ ትምህርት ተግባራት ጋር በተያያዘ በኮሌጁ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሠራተኛ ነው::
2. "የአስተዳደር ሠራተኛ" ማለት የአካዳሚክ ሠራተኛ ያልሆነ ማንኛውም የኮሌጁ ሠራተኛ ነው::
3. "ቢሮ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ ነው::
4. "የጤና ሙያ" ማለት በክልሉ ውስጥ በሚገኙ የጤና ባለሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት አማካኝነት በነርስነት፣ በፋርማሲ ቴክኒሻንነት፣ በላቦራቷር ቴክኒሻንነት እና በሌሎች ተመሳሳይ መስኮች በሚካሄድ ስልጠና የሚገኝ ልዩ ዕውቀት ሲሆን ትርጓሜው የባለሙያውን ክህሎትና አመለካከት ይጨምራል::
5. "የጤና ባለሙያ ሥልጠና" ማለት በልዩ ልዩ የጤና ሙያ መስኮች በመደበኛ ወይም መደበኛ ባልሆነ የአሰለጣጠን ስልት በተለያዩ የጊዜ ርዝማኔዎች በቅድመ ሥራ ወይም በሥራ ላይ ስልጠና መርሀ-ግብር የሚሰጥና ከሰርተፊኬት እስከ ዲፕሎማ የሚያስገኝ ትምህርት ወይም ስልጠና ነው::

regulation:

1. "Academic employee" means any employee of the College engaged in teaching, research and curricular activities related thereto.
2. "Administrative employee" means any employee of the college who is not member of the academic staff.
3. "Bureau" means the Amhara National Regional State Health Bureau.
4. "Health profession" means a special expertise in nursing, techniques of pharmacy and laboratory as well as other similar streams gained through trainings conducted in the Health Profession Training Institutions of the Regional State including the skills and outlook of the professional.
5. "Health professional training" means education or training given in various streams of the health profession either in formal or non-formal training methods, be it in pre-service or in-service training programs for different lengths of time so as to enable one obtain a certificate up to diploma.

## ክፍል ሁለት
## ስለደብረ ብርሃን ጤና ሣይንስ ኮሌጅ መቋቋም፣ ተጠሪነትና የሥራ ድርሻ

## PART TWO
## ESTABLISHMENT, ACCOUNTABILITY AND DUTIES OF THE DEBRE BERHAN HEALTH SCIENCE COLLEGE

### 3. መቋቋምና ተጠሪነት

1. የደብረ ብርሃን ጤና ሣይንስ ኮሌጅ ከዚህ

### 3. Establishment and Accountability

1. The Debre Berhan Health Science College,

በኋላ "ኮሌጁ" እየተባለ የሚጠራ ሕጋዊ ሰውነት ያለው፣ ራሱን የቻለና በመካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ አንድ የክልሉ የትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል::

2. የኮሌጁ ተጠሪነት ለቢሮው ይሆናል::

/hereinafter referred to as/ "The College" is hereby established as an autonomous and middle-level educational institution of the regional state, having its own legal personality, pursuant to this regulation.

2. The accountability of the college shall be to the Bureau.

## 4. ዓላማ

የኮሌጁ አላማ በክልሉ ውስጥ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ስልትን በመንደፍ የህብረተሰቡን የጤና ችግር መቅረፍ የሚችሉ፣ የጋራ አሰራርን የሚከተሉ ብቃት ያላቸውና በሙያ ስነ-ምግባር የታነጹ የመካከለኛ ደረጃ የጤና ባለሙያዎችን ማፍራት ነው::

## 4. Objective

The objective of the college is to produce middle level health professionals who are capable of solving health problems of the society and following up the principle of teamwork, as well as who are efficient and equipped with professional ethics by designing working procedures that might facilitate the prevention and thereby control of diseases in the Regional state.

## 5. የኮሌጁ ዋና አድራሻ

የኮሌጁ ዋና አድራሻ በደብረ ብርሃን ከተማ ይሆናል::

## 5. Principal Address of the College

The principal address of the college shall be the town of Debre Brhan.

## 6. የኮሌጁ ተግባርና ኃላፊነት

ኮሌጁ በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል:-

1. በተለያዩ የጤና ሙያ መስኮች ደረጃውን የጠበቀ ሥልጠና በመስጠት ብቃት ያላቸው የመካከለኛ ደረጃ የጤና ባለሙያዎችን የማፍራት ኃላፊነትን የሚያረጋግጥና ሀገር አቀፍ ደረጃን መሠረት ያደረገ የትምህርት፣ የሥልጠናና የምርምር መርሃ ግብር ይቀይሳል፣ በቢሮው

## 6. Duties and Responsibilities of the College

The College shall, pursuant to this regulation, have the following duties and responsibilities:

1. Devise education, training and research programs responsive to the national standard with the view to ensuring the production of efficient, middle-level professionals in various health profession streams and implement same up on approval by the Bureau;

ሲፀድቅለትም በስራ ላይ ያውላል፤

2. ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ሠልጣኞችን ይቀበላል፤
3. የተመዘገቡበትን የጤና ሙያ ስልጠና በብቃት ላጠናቀቁ ሰልጣኞች እንደአግባብነቱ ዲፕሎማ ወይም የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
4. የክልሉን ፍላጐት መሠረት ያደረገና በጤናው መስክ ላይ ያተኮሩ ሴሚናሮችን፣ አጫጭር ሥልጠናዎችን፣ አውደጥናቶችንና ሲምፖዚየሞችን ያዘጋጃል፣ ያካሂዳል፤
5. ለኮሌጁ ስራ የሚያገለግሉና ከጤና ሙያ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ትምህርታዊ ፅሁፎችንና ጆርናሎችን ያዘጋጃል፣ እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ያሣትማል፣ ያሠራጫል፤
6. ለሠልጣኞች የሙያዊ አመራርና የምክር አገልግሎቶችን ያመቻቻል፤
7. በቢሮው ክትትል የመካከለኛ ደረጃ የጤና ሙያ ስርዓተ-ትምህርት ማቴሪያሎችን ያዘጋጃል፣ ያሻሽላል፤
8. የተግባራዊ ልምምድ ፕሮግራሞችን ይመራል፣ ያስተባብራል፤
9. የድህረ ስልጠና ክትትል ሥራዎችን ያካሂዳል፣ ይከታተላል፣ ተሞክሮዎችን ተጠቅሞ የስልጠናውን ሂደት ያጐለብታል። ወቅታዊና አስፈላጊ ሪፖርቶችን ያቀርባል፤
10. ተመሣሣይ ዓላማ ካላቸው ከአገር ውስጥም ሆነ በቢሮው አማካይነት ከውጭ አገር የጤና ኮሌጆች ጋር የሥራ ግንኙነቶችን ይመሠርታል፤
11. የሰው ኃይል ፍላጎትን መሠረት ያደረጉ የገበያ ጥናቶችን በማካሄድና በክልሉም ሆነ

2. Admit trainees in accordance with a directive to be issued by the Bureau;
3. Award diplomas or certificates, as deemed necessary, for those trainees who may have successfully completed the health profession training for which they had been registered.
4. Prepare and undertake seminars, short-term trainings, workshops and symposia depending on the interests of the regional state and focusing on the streams of the health profession
5. Prepare, cause the preparation of, have published and distributed educational articles and journals related to the health profession for the service of the College;
6. Facilitate professional guidance and counseling services for the trainees,
7. Prepare and improve the middle-level health professionals' curricular material with the follow up of the Bureau;
8. Direct and coordinate apprenticeship programs;
9. Carry out post training follow up activities, monitor same and improve the training process depending on the experiences as well as submit periodic and vital reports;.
10. Create working relationships with domestic, and through the Bureau, with foreign health colleges having similar objectives;
11. Carry out and direct the education and training activities by undertaking market

በፌዴራሉ መንግስት ደረጃ እየተጠኑ በሚወጡ ወጪን የመጋራት ፖሊሲዎችና የማስፈፀሚያ ስልቶች መሠረት የትምህርትና የሥልጠና ተግባራትን ያከውናል፣ ይመራል፤

12. ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የክልሉ መስተዳደር ም/ቤት በሚወስነው መሰረት ተገቢውን ዋጋ ያስከፍላል፣ በዓላማው ላይ ተመስርቶም የውስጥ ገቢውን በየጊዜው ያዳብራል፤

13. የምልመላ፣ የሥልጠናና የምሩቃንን የሥራ ስምሪት እየተከታተለ በሚገኙት መረጃዎች መሠረት የሥልጠናውን ሂደት ያስተካክላል፤

14. የአሰለጣጠን ሂደቱ ግልፅ፣ ቀልጣፋና ፍትሃዊ ይሆን ዘንድ ሠልጣኞች የአካዳሚክና የአስተዳደር ሠልጣኞች የሚገመግሙበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደርጋል፤

15. ኮሌጁን የሚያማክርና የሚደግፍ የትምህርትና ስልጠና ቦርድ ያቋቁማል፤

16. ከመንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ከግል ባለሃብቶችና ከሲቪክ ተቋማት ጋር የጠበቀ የሥራ ግንኙነት ይፈጥራል፤

17. የህብረተሰቡን የጤና ችግር ሊቀርፉ የሚችሉ ልዩ ልዩ የምርምር ተግባራትን ያካሂዳል፤

18. የሚፈቀድለትን በጀትና የሚመደብለትን የሰው ኃይል በአግባቡ ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

19. ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣

studies as may be necessitated by the needs for manpower and in accordance with the cost-sharing polices and implementation strategies to be issued by the Regional or Federal Governments.

12. Collect appropriate Charges for the services it renders pursuant to the decision of the Council of the Regional Government and thereby increase its internal revenue from time to time;

13. Follow up the selection, training and employment opportunities of graduates and improve the process of training on the basis of the data obtained therefrom;

14. Put in place and effectuate a system of evaluation of the academic and administrative staff by the trainees with the view to making the training process transparent, efficient and just;

15. Establish an education and training board which advises and supports the college;

16. Create strong working relationships with governmental and non-governmental organizations as well as private investors and civic institutions;

17. Undertake various research activities that may be able to solve the health problems of the society;

18. Properly manage and administer the budget appropriated for and manpower allocated to it;

19. Enter into contracts, own property as well as

የንብረት ባለቤት ይሆናል፣

20. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያግዙ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል::

## ክፍል ሦስት
## ስለኮሌጁ አደረጃጀትና አመራር

### 7. የአካዳሚክ ኮሚሽን

የኮሌጁ አካዳሚክ ኮሚሽን በዚህ ደንብ መሠረት ተጠሪነቱ ለቢሮው ሆኖ ከዚህ በታች የተመለከቱት አባላት ይኖሩታል:-

1. የኮሌጁ ዲን ---------------------------- ሰብሳቢ
2. የኮሌጁ ምክትል ዲኖች -------------- አባላት
3. የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች ---------- አባላት
4. የኮሌጁ ሬጂስትራር ------------------- አባል
5. የተማሪዎች አመራርና የሙያ አማካሪ -------------------------------------------------- አባል
6. የኮሌጁ ሴት መምህራን አንድ ተወካይ --------------------------------------------------- አባል
7. የተማሪዎች መማክርት አንድ ተወካይ -------------------------------------------------- አባል
8. የሴት ሠልጣኞች አንድ ተወካይ ------- አባል
9. የኮሌጁ ፕላንና ፕሮግራም ኦፊሰር-------------------------------------------- አባልና ፀሐፊ::

### 8. የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር

የኮሌጁ አካዳሚክ ኮሚሽን በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. የኮሌጁ የትምህርት፣ የስልጠናና የምርምር ፕሮግራሞች በቢሮው በሚወጣ መመሪያ

sue and be sued in its own name;

20. Perform such other related functions as may be helpful to accomplish its objective.

## PART THREE
## ORGANIZATION AND MANAGEMENT OF THE COLLEGE

### 7. The Academic Commission

The academic commission of the college shall, pursuant to this regulation, be accountable to the Bureau and have the following members:

1. The dean of the college ---------- chair person;
2. The vice deans of the college ------- members;
3. The heads of departments ------------ members;
4. The registrar of the College ----------- member;
5. Students' guidance and professional counsellor --------------------------------------------- member;
6. A representative of female instructors of the College ---------------------------------- member;
7. A representative of the students' council--- member;
8. A representative of female trainees --- member;
9. The Planning and program officer of the College ------------------ member and secretary.

### 8. Powers and Duties of the Commission

The academic commission of the College shall, pursuant to this regulation, have the following powers and duties:

1. Ascertain that the education, training and research programs of the College are prepared

መሠረት መዘጋጀታቸውን ያረጋግጣል፤

2. ኮሌጁ ለሚሰጠው የምስክር ወረቀትና ዲፕሎማ የሚያስፈልገውን የሥልጠና ፕሮግራምና የተለያዩ ኮርሶች የሚኖራቸውን ዋጋና የክሬዲት መጠን ይወስናል፤
3. ቢሮው የሚያወጣው መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሌጁ የሚቀበላቸው ተማሪዎች በየሥልጠና መስኩ የሚደለደሉበትን ሥርዓት ይወስናል፤
4. የሥልጠና ዘዴው በየጊዜው የሚሻሻልበትን ስልት ይቀይሣል፤
5. የፈተና አሰጣጥ ዘዴዎችን፣ የሠልጣኞችን የፈተና ውጤቶችና የደረጃ ሽግግር በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፣ በሥራ ላይ ያውላል፤
6. የኮሌጁን ተማሪዎች የዲስፕሊን መመሪያ ያወጣል፣ የተማሪ ቅበላን፣ መልሶ ቅበላንና በአካዳሚክ ምክንያት የሚወሰን ስንብትን መርምሮ ያፀድቃል፤
7. ሥልጠናቸውን ጨርሰው መመረቅ ለሚገባቸው ሠልጣኞች ኮሌጁ እንደ አስፈላጊነቱ ዲፕሎማ ወይም የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ይወሰናል፤
8. የአሰራር ሞዳሊቲዎችን እያወጣ የመካከለኛ ደረጃ የጤና ሙያ ስርዐተ ትምህርት ዝግጅትና የማሻሻል ስራዎችን ያካሂዳል፤
9. በአካዳሚክ ሠራተኞች አስተባባሪነት የሚከናወኑትን የተግባራዊ ልምምድ ፕሮግራሞችና የድህረ ሥልጠና ክትትል ስራዎች ተፈፃሚነት ይገመግማል፤
10. ለኮሌጁ የሚከፈሉ የትምህርትና የሌሎች

incompliance with the directive issued by the Bureau;

2. Determine the educational program, the value of different courses as well as the number of credit hours required for the certificate and diploma to be awarded by the College;
3. Without prejudice to the directive to be issued by the Bureau, determine the system whereby students admitted by the College may be assigned into its various educational streams;
4. Devise a mechanism through which the training method may be improved from time to time;
5. Issue guidelines concerning the methods of administering examinations, maintenance of student examination results as well as devise a promotion system and put same into effect;
6. Formulate and issue a set of disciplinary rules governing the students of the College, examine and approve submissions with respect to admission, re-admission and academic dismissals thereof;
7. Decide that the college should award diploma or certificate, as may be necessary, to those students who may have completed their training and deserve graduation;
8. Carry out middle-level health profession curriculum preparation and review activities by presetting working modalities;
9. Evaluate the implementation of practicum programs and post-training follow -up activities carried out with the coordination of the academic staff;
10. Study the rate of education fee and other

አገለግሎቶች ክፍያዎችን ተመን አጥንቶ ያስወስናል፤

11. በዲኑ ተጠንተው የሚቀርቡለትን የአካዳሚክ ሠራተኞች እድገት፣ ማዕረግና ሽልማት በተመለከተ የበኩሉን የውሣኔ ሃሣብ እየሰጠ በቢሮው ያስፀድቃል፤

12. የኮሌጁ የአካዳሚክ ሠራተኞች የሚተዳደሩበትን መመሪያ አዘጋጅቶ ለቢሮው በማቅረብ ሲፈቀድ በሥራ ላይ ያውላል፤ ብቁ ለሆኑት የአካዳሚክ ሠራተኞች የኮንትራት ውል እንዲታደስ ያደርጋል፣ የአስተዳደር ሠራተኞም በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ሕጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መተዳደራቸውን ያረጋግጣል፤

13. ኮሌጁ በአገሪቱ ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና አግባብ ካላቸው መንግሥታዊና የግል ድርጅቶች ጋር የሚኖረው የሥራ ግንኙነት የሚጠናከርበትን መንገድ ይቀይሣል፤

14. አዳዲስ የሚከፈቱና የሚዘጉ የጤና ሙያ ሥልጠና ዘርፎችን አጥንቶና ለይቶ ለቢሮው ለውሣኔ ያቀርባል፤

15. ከኮሌጁ የሥራ አመራር ጋር ተባብሮ ይሠራል፤

16. የተለያዩ የጤና ሙያ የሥልጠና ሞጁዩሎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤

17. ኮሌጁን በሚመለከቱ ጉዳዮች እየመከረ የፖሊሲ ሃሣብ ያመነጫል፤

18. የኮሌጁ አሠልጣኝ መምህራን ሙያቸውን እንዲያሻሽሉ የሥልጠና ስልቶችን ይቀይሣል፣

service charges to be paid to the college and have same determined thereof;

11. Draw up proposals with regard to career promotion, ranks and prize awards of the academic staff as studied by the Dean and submit same to the Bureau for approval with its own recommendations;

12. Prepare the administrative manual governing the academic staff of the College, submit it to the Bureau and implement same upon approval; cause the renewal of the contract of those academic staff competent in the career and ensure that the administrative employees are managed pursuant to the Regional Civil Service laws, regulations and directives;

13. Set out ways to strengthen working relationship of the College with other higher educational institutions as well as relevant public and private organizations within the country;

14. Study and identify the health professionals' training streams to be newly opened and/or closed down and submit same to the Bureau for approval;

15. Work in collaboration with the management of the college;

16. Cause the preparation of various health professionals' training modules;

17. Deliberate on issues pertaining to the College and thereby generate policy proposals to that effect;

18. Devise training strategies and thereby create an enabling environment so that trainer-

ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

19. የኮሌጁን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል::

## 9. የትምህርት ክፍሎች አደረጃጀትና ተዋፅኦ

1. ኮሌጁ በየሥልጠና ዘርፉ የሚደራጁ የትምህርት ክፍሎች ይኖሩታል፤
2. እያንዳንዱ የትምህርት ክፍል የክፍሉን የአካዳሚ ሠራተኞች በሙሉ በአባልነት የያዘ ሆኖ ስብሰባዎችን የየትምህርት ክፍሉ ኃላፊዎች በሰብሳቢነት ይመራሉ::

## 10. የትምህርት ክፍሎች ተግባርና ኃላፊነት

የትምህርት ክፍሎች በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሯቸዋል:-

1. በኮሌጁ ለሚሰጠው የምስክር ወረቀትና ዲፕሎማ የሚያስፈልገውን የትምህርት ፕሮግራምና የተለያዩ ኮርሶች የሚካሄዱበትን የጊዜ ሰሌዳ በሚመለከት ለአካዳሚክ ኮሚሽኑ ሃሣብ ያቀርባሉ፤
2. በተለያዩ የጤና ሙያ መስኮች አዳዲስ የሥልጠና ሞዱዩሎችን እያዘጋጁና በአካዳሚክ ኮሚሽኑ እያስፀደቁ ተግባራዊ ያደርጋሉ፤
3. የሥልጠና ዘዴዎች ስለሚሻሻሉበት ሁኔታ ለአካዳሚክ ኮሚሽኑ ሃሣብ ያቀርባሉ፤
4. ወደየትምህርት ክፍሉ ሊደለደሉ ስለሚገባቸው ሠልጣኞች ለአካዳሚክ ኮሚሽኑ ሃሣብ ያቀርባሉ፤

instructors of the college would improve their professional competence;

19. Carry out such other related functions as may assist the attainment of the objective of the College.

## 9. Organization and Composition of the Departments

1. The college shall have various departments organized in different training streams.
2. Each department shall consist of all the department's academic employees in membership and the head of such a department shall preside over its meetings.

## 10. Duties and Responsibilities of the Departments

The departments shall, Pursuant to this regulation, have the following duties and responsibilities:

1. Put forward proposals to the academic commission as to the education program necessary to award certificate and diploma by the college and with respect to the timetable in which the various courses are given thereof;
2. Prepare up-to-date training modules in various health profession streams and implement same upon approval by the academic commission;
3. Propose ways to the academic commission in which the training methods may be improved;
4. Propose to the academic commission as to the possible assignment of those trainees deserving same into the departments

www.chilot.me

5. በየክፍሉ ለተደለደሉ ሠልጣኞች አማካሪዎችን ይመድባሉ፣ ሰልጣኞች ተገቢውን የማማከር አገልግሎት ማግኘታቸውንም ያረጋግጣሉ፤
6. የትምህርት ክፍሎቹን የሚመለከቱ የአካዳሚክ ችግሮች የሚፈቱበትን ሁኔታ በሚመለከት ለአካዳሚክ ኮሚሽኑ ሃሣብ ያቀርባሉ፤
7. ለየትምህርት ክፍሉ መምህራን የኮርስ ድልድል ያደርጋሉ፣ የፈተናዎችን ዝግጅትና አፈፃፀም ያስተባብራሉ፤
8. የየራሳቸውን የመተዳደሪያ መመሪያ አውጥተው ለአካዳሚክ ኮሚሽኑ ያቀርባሉ፣ ሲፈቀድላቸውም በሥራ ላይ ያውላሉ፤
9. የየትምህርት ክፍሉን የስርዐተ ትምህርት ዝግጅትና የማሻሻል ስራዎች ያከናውናሉ፤
10. የትምህርት ክፍሎችን በሚመለከቱ ሌሎች የአካዳሚክ ጉዳዩች ላይ የበኩላቸውን አስተያየት ይሰጣሉ::

## 11. ስለኮሌጁ ዲን

ኮሌጁ በቢሮው አቅራቢነት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሾሙ ዲንና ምክትል ዲኖች ይኖሩታል::

## 12. ስለዲኑ ተጠሪነትና ሥልጣን

የኮሌጁ ዲን ተጠሪነቱ ለቢሮው ሆኖ:-

1. የኮሌጁ ዋና አስፈፃሚ በመሆን ይሰራል፣ ከቢሮው በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት ኮሌጁን ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

concerned;

5. Assign advisors to the trainees of each department and thereby ensure that the trainees are provided with the appropriate advisory service;
6. Propose to the academic commission as to the possible solution of academic problems pertaining to the departments;
7. Allocate courses among instructors of each department and coordinate the preparation and execution of examination activities;
8. Issue their own by-laws and implement same upon approval by the academic commission;
9. Carry out curriculum preparation and improvement activities of each department.
10. Render their opinions with regard to other academic matters pertaining to the departments.

## 11. The Dean of the College

The college shall have its own dean and vice deans to be appointed by the Head of the Regional Government upon their presentation by the Bureau.

## 12. Accountability and Powers of the Dean

Having been accountable to the Bureau, the dean of the college shall:

1. Work as a chief executive of the college and, in accordance with the general directive handed down to him by the Bureau, direct, administer and supervise

2. በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 ሥር የተመለከቱትን የኮሌጁን ተግባርና ኃላፊነቶች በሥራ ላይ ያውላል፤
3. የኮሌጁን የአካዳሚክና የአስተዳደር ሠራተኞች በዚህ ደንብ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 12 በተጠቀሰው መሠረት ያስተዳድራል፤
4. የኮሌጁን የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የስራ እቅድና የማስፈፀሚያ በጀት ረቂቅ አዘጋጅቶ ለአካዳሚክ ኮሚሽኑ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
5. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ኮሌጁን ይወክላል፤
6. ስለኮሌጁ የሥራ እንቅስቃሴ በየሩብ አመቱ ለቢሮው ሪፖርት ያቀርባል፤
7. ለሥራው ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ተግባርና ኃላፊነቱን በከፊል ለኮሌጁ የበታች ስራ ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤
8. በዲስፕሊን ጉዳዮች ምክንያት የሚቀርቡ የውሣኔ ሃሣቦችን መርምሮ ያፀድቃል፤
9. በተግባራዊ ልምምድ ከሚሣተፉ የተለያዩ ድርጅቶችና መ/ቤቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ሥልጠናው እንዲጠናከር ያደርጋል፤
10. ለኮሌጁ ትምህርትና ስልጠና ቦርድ በፀኃፊነት ያገለግላል::

## 13. የአካዳሚክ ምክትል ዲን ተጠሪነትና ሥልጣን

የኮሌጁ የአካዳሚክ ምክትል ዲን ተጠሪነቱ ለዲኑ ሆኖ፡-

over the institution thereof;

2. Put into effect the duties and responsibilities of the College as are outlined under article 6 of this regulation hereof;
3. Administer the academic and administrative staff of the College pursuant to the provisions of Art.8, sub-art. 12 of this regulation;
4. Prepare drafts of short, medium and long-term plans and implementation budget of the College, submit them to the academic commission and effectuate same upon approval thereof;
5. Represent the College in all its relations with third parties;
6. Submit quarterly reports to the Bureau with regard to the activities of the college;
7. Be able to delegate part of his duties and responsibilities to the subordinate heads and other employees of the Collage to the extent necessary for the effectiveness of the task;
8. Examine and approve proposals on the disciplinary matters submitted to it;
9. See to it that trainings are strengthened by creating relationships with various organizations and offices participating in apprenticeship programs;
10. Serve the education and training board of the college in a secretarial capacity.

## 13. Accountability and Powers of the Academic Vice Dean

Having been accountable to the dean, the academic vice dean of the college shall:

1. በቢሮው በሚሰጠው እቅድ መሠረት የጤና ሙያ ስርዓተ-ትምህርት ዝግጅትና የማሻሻያ ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፣ በወቅቱም ለቢሮው እንዲደርስ ያደርጋል፤
2. የኮሌጁን አካዳሚ ሥራዎች፣ የአካዳሚክ ኮሚሽኑን ውሣኔዎች እና እንዲሁም አካዳሚክ ነክ ደንቦችና መመሪያዎችን ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፤
3. የአካዳሚክ ጉዳዩችን በሚመለከት ዲኑን ያማክራል፣ በቅርብ ይረዳል፤
4. ኮሌጁ የሚሰጣቸው ሥልጠናዎች በአካዳሚክ ኮሚሽኑ በፀደቀው የትምህርት ካሌንደር መሠረት መካሄዳቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤
5. የሥልጠናውን ሂደት ለማቀላጠፍ አስፈላጊ የሆኑ አቅርቦቶችና አገልግሎቶች እንዲሟሉ ያደርጋል፤
6. የአካዳሚክ ሠራተኞች በተለያዩ የሥልጠና መስኮች የሚያዘጋጁቸውን አጫጭር የሥልጠና ሞዲዩሎች የዝግጅት ሂደት በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤
7. በዲኑ ወይም በአካደሚክ ኮሚሽኑ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤
8. ዲኑ በማይኖርበት ወይም መደበኛ ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሠራል።

## 14. የኮሌጁ የልማትና ምርምር ምክትል ዲን ተጠሪነትና ተግባር

1. Supervise over, coordinate, follow up and execute health profession curriculum preparation and improvement activities pursuant to the plan given to him by and submit same to the Bureau;
2. Follow up the academic activities of the college and execute the decisions of the academic commission as well as those regulations and directives relating to academic matters;
3. Advise and closely assist the dean with regard to academic matters;
4. Follow up and ensure that the training activities of the college are carried out in accordance with the calendar adopted by the academic commission;
5. Cause the fulfillment of supplies and services necessary to facilitate the training process;
6. Direct and coordinate the preparatory process of short training modules prepared by the academic staff in various training streams;
7. Perform such other functions as are specifically assigned to him by the dean or the academic commission;
8. Act on behalf of the dean in his absence or under the circumstances where he is unable to perform his normal duties.

## 14. Accountability and Powers of the Development and Research vice Dean of the college

የኮሌጁ የልማትና ምርምር ምክትል ዲን ተጠሪነቱ ለዲኑ ሆኖ፡-

1. የኮሌጁ መምህራን የጥናትና ምርምር ሥራዎችን እንዲያካሂዱ ያስተባብራል ፣
2. የኮሌጁን ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ፕሮግራሞች ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣
3. የድህረ ስልጠና ክትትልን በተመለከተ ኮሌጁ የሚሰጠው ስልጠና ያለበትን ጥንካሬና ድክመት በመለየት ብቃት ያለው ስልጠና ለመስጠት የሚያስችለውን መጋቢ ሃሳብ የሚያስገኝ መሆኑን በመረዳት በአግባቡና በታለመለት ጊዜ እንዲካሄድ ያደርጋል፤
4. የምርምርና የስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ሥራዎች በወጣላቸው እቅድ መሠረት መካሄዳቸውን ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፤
5. የኮሌጁን የሰው ሃይል፣ የእቃ ግዥ፣ የንብረትና የጠቅላላ አገልግሎቶች፣ አስተዳደር እንዲሁም የሂሳብና የበጀት ጉዳዮችን ያቅዳል፣ ይከታተላል፣ ይመራል፣ አፈፃፀማቸውን ይቆጣጠራል፤
6. የኮሌጁ የውስጥ ገቢ የሚዳብርበትንና የሚተዳደርበትን መንገድ ያጠናል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
7. የልማትና የምርመር ጉዳዮችን በሚመለከት ዲኑን ያማክራል፣ ይረዳል፤
8. በዲኑ እና በአካዳሚክ ኮሚሽኑ የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል፡፡

Having been accountable to the Dean, the Development and Research Vice Dean of the College shall:

1. Coordinate the instructors of the college to undertake study and research activities;
2. Coordinate and follow up the experience-sharing and practicum programs of the college;
3. Cause the undertaking of post-training follow up and tracer study properly and at planned times so as to get an invaluable feedback which would enable one to provide an effective training by identifying the strengths and weaknesses of the trainings given in the college;
4. Follow up and execute that the research activities and curriculum preparations are carried out in accordance with the plans adopted thereof;
5. Plan, follow-up and direct the administration of personnel, procurement, property and general services as well as accounting and budgetary matters and thereby supervice over the execution thereof;
6. Study the ways in which to increase and administer the internal revenue of the college and implement same upon approval;
7. Advise and assist the dean with regard to development and research matters;
8. Perform such other functions as may be given to him by the dean and the academic commission.

www.chilot.me

## 15. የኮሌጁ ሌሎች የአካዳሚክ ክፍል ኃላፊዎች

የኮሌጁ ሌሎች ልዩ ልዩ የአካዳሚክ ክፍል ኃላፊዎች ቅጥር፣ ምደባ፣ የሥራ ድርሻና መሰል አስተዳደራዊ ጉዳዮች በቢሮው በሚወጣና ለክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ቀርቦ በሚፀድቅ መመሪያ መሠረት የሚወሰን ይሆናል::

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 16. በጀት

የኮሌጁ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኝ ይሆናል:-

ሀ. የክልሉ መንግስት የሚመድበው በጀት:

ለ. ኮሌጁ በትምህርትና ስልጠና ረገድ የሚሰበስበው የአገልግሎት ክፍያ፤

ሐ. በስጦታም ሆነ በእርዳታ የሚገኝ የዓይነትና የጥሬ ገንዘብ ሀብት፣

መ. ሌሎች የውስጥ ገቢዎች::

## 17. የሂሣብ መዛግብትና ኦዲት

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 16 ስር የተመለከተው ገንዘብ በኮሌጁ ስም በሚከፈት የባንክ ሂሣብ ተቀማጭ ሆኖ የኮሌጁን ዓላማ ለማስፈፀም በየጊዜው ወጭ የሚደረግ ይሆናል::

2. ኮሌጁ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብና

## 15. Other Academic Heads of the College

The recruitment, assignment, duties and the like matters concerning other various academic division heads of the College shall be determined pursuant to the directive to be issued by the Bureau and approved by the Regional Civil Service Commission.

## PART FOUR
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 16. Budget

The budget of the college shall be drawn from the following sources:

a. Budget which the Regional Government allocates;

**b.** Tuition fees to be collected by the college;

c. Resource in kind and cash to be obtained in the form of gifts or aid;

d. Other internal revenues.

## 17. Books of Account and Auditing

1. The amount of the budget indicated under Art. 16 of this regulation shall be deposited in a bank account to be opened by the College and withdrawn from time to time with the view to accomplishing the objective of same.

2. The college shall keep books of account

የንብረት መዛግብትን ይይዛል።

3. የኮሌጁ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መ/ቤት ወይም ቢሮው በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየጊዜው ይመረመራሉ።

## 18. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጐች

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## 19. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ቢሮው ይህንን ደንብ በተሟላ ሁኔታ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች የማውጣት ስልጣን አለው።

## 20. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር

ሚያዝያ 3 ቀን 1997 ዓ.ም

ዮሴፍ ረታ

የአማራ ብሔራዊ ክልል

ርዕሰ መስተዳድር

and records of property which are accurate and complete thereto.

3. The books of account as well as other financial and property documents of the College shall be audited at any time by the office of the Auditor General of the Regional State or other auditors designated by the Bureau.

## 18. Inapplicable Laws

Any other regulation, directive or customary practice inconsistent with this regulation may not apply to matters provided for in this regulation.

## 19. Power to Issue Directives

The Bureau shall have the power to issue directives necessary for the full implementation of this regulation.

## 20. Effective Date

This regulation shall come in to force as of the day of its publication in the Zikre Hig Gazette of the Regional state.

**Done at Bahir Dar**

**This 11th day of April, 2005**

**YOSEF RETA**

**Head of Government of the Amhara National Regional State**